# አሞራው በረረ...

በዚያ በቀውጢ ቀን
ጫካውን መንጥረን፣ ዕንጨቱን ሰንጥቀን
ጉደጓዱን ቆፍረን፣ዓለቱን ፈልቅቀን
በፍርሓት ሰቀቀን፣
ታምቀን... ተደብቀን...
ኣሞራና ቅሉ፣ በኣየር ሲዋልሉ
ፍየሏም ስትቃርም ቅጠላ-ቅጠሉ
ከገደል፣ ካፋፉ
ሲምቦገቦግ መድፉ
ቀትሩ ጨልሞብን
ከበላያችን ላይ ሞት ሲያንዣብብን...

ቅጠሉና ቅሉ ሰርክ ሲተፋፈሩ፣
ፍየልና ነብሩም ሲፋቀሩ፣
ኣሞራና ሳሩ ሳይነጋገሩ፣
ከሩቁ ሲናናቁ፣ ሳይከባበሩ
ሁሉም ሲፈሩ፣ ሲጠራጠሩ...
በሸለቆው ሲኖሩ ነበሩ።

ነገሩ ኣለፈና፣ ሰላም ሰፈነና...
ደጉ ዘመን መጥቶ ሁሉም ተረሳና
ኣሞራና ፍየል ሲሳለቁ
ነብርና ቅልም ሲሳሳቁ
ኩኩሉ! ኣልነጋም! ሲደበቁ
ሲያፌዙ፣ ሲስቁ...
ስዓቱን ኣያውቁ!

ኣፍ የሰጠው ሁሉ ሞልቶ ተናገረ
በልቶ የጠገበውም ርሃብ ኣማረረ
ወንዱም፣ ሴቱም ዛሬ በጆሮ ኩትቻ
ኣንደበትን ስሎ በቃላት ሽኩቻ
መላ ዕውቀታቸው ሆኗል ምላስ ብቻ!
ሰውና ኣሻንጉሊት ባጌጠበት ዘመን
ሕልምና ቅዠቱ የቀትር ሰመመን
የቱ ጮማ ስጋ፣ የትኛው ነው ጐመን?
ሁሉም ጀግና ይመስላል
ኣለሁ! ኣለሁ! ይላል...
በምን ተለክቶ፣ በመንስ ሊተመን?
ቁርጡ የመጣ ዕለት
ሓቁ ሊለይለት!
ጊዜ ሲቀናለት ሁሉም ይመቻቻል
ርሃብ ምን ኣባቱ፣ ጥጋብ ነው እማይቻል!

ቅሉ ዋሽንት ሆኖ ሲያፏጭ፣ ሲያስካካ
ኣሞራው ከቅጠል እስክስታ ሲያስነካ
ፍየሉም ከነብር ቁመት ሲለካካ
በከንቱ! ያለ ኣግባብ!
ወይ ጥጋብ! ወይ ጥጋብ!
ቁርጡ የመጣ ዕለት
ለቁልቢ ስለት...












ሲፋቀሩ ዋሉ ቅጠልና ቅሉ
ሲያወሩ በኣንድነት ነብርና ፍየሉ
ኣሞራና ቅል ግን ሳይነጋገሩ
ምስጢሩንም እንጃ እየትፋፈሩ
ሁሌ ሲናናቁ፣ ሳይከባበሩ፣
የሽሙጥ፣ የጐሪጥ፣ ሳይደፋፈሩ፣
ለረዥም ዘመናት እንዲያ ሆነው ቀሩ።

እንዴት ብሎ ታድያ ነገር ተበላሸ?
ነብሩ ሞኝ ይመስል ዓይኑን እያሻሸ
"እህቴ!እህቴ!" ብሎ እያሞካሸ
ገራገር በመምሰል ፍየልን ጠራና
"ነዪ ምሪኝ!" ኣላት ዓይኑን ጨፈነና
ኣሞራም ቅል ኣቅፎ ከበሮ መታና
ሁሉም ቁጤማውን ከመሬት ነስንሰው
ሲጠጡ ኣደሩ የስለት ያለኸው!
ስካር መጥፎ ኣመል...
ወይ ፍየል! ወይ ቅጠል!
ዳንኪራ ሲረግጡ፣ ሁሉም ሲጨፍሩ
ኣይነጋ መስሏቸው ሲያስካኩ ኣደሩ።



ሌሊቱም ቢጨልም ጨረቃዋ ደምቃ
ፍየልም ስትስቅ ጥርሷ እስኪነቃ
ሲደለቁ ኣደሩ ዘፈኑ እስኪያበቃ
ሁሉም ያልፋልና ማለዳ ሲነጋ
ኣሬራ፣ ብጥብጥ ነው፣ ፍቅሩ መቸ ረጋ!



በተንኰል፣ በጉልበት ኣንዱ ካንዱ በልጦ
ዘረገፈው እንጂ ከመሬት ዘርጥጦ
ቁጤማው ደም ለብሶ፣ ጭቃ ተለውሶ
ነብሩም ሆዱ ሞልቶ ድንጋይ ተንተርሶ...
ፍየል የት ደረሰች? ስጋዋ ተልጦ
ብጥስጥሷ ወጥቷል ዓጥንቷ ተግጦ።



እንዲህ ያለ ፍቅር፣ ኣይነሳ ይቅር
የኣሞራና የቅል፣ የፍየል፣ የነብር
ከጥንት የቆየ ነው ሲባል የነበረ፡
"ኣሞራው በረረ
ቅሉም ተሰበረ!"

ገ/ኢ. ጐርፉ።